# በ“መድረክ” ዙሪያ የቀረቡ አስተያየቶች

ግርማ ካሳ
muziky68@yahoo.com

የካቲት 27 2001

ይህንን መጣጥፍ እንድጽፍ ያነሳሳኝ ሰሞኑን “መድረክ” ተብሎ ይታወቅ ከነበረዉ አካል ጋር የአንድነት ፓርቲ አብሮ ለመሥራት መወሰኑን በተመለከተ፣ አከራካሪ ዉዝግቦች በመነሳታቸዉ ነዉ። በተለይም በዳይስፖራዉ ይህ “መድረክ” የሚለዉ ነገር ያልተዋጠላቸዉ አንዳንድ ወገኖች የቅሬታ ድምጻቸዉን በጣም እያሰሙ ይገኛሉ።

ስለመድረክ አስተያየት ከመስጠቴ በፊት የተወሰኑ መሰረታዊ ጭብጦችን በማንሳት ሁላችንም የጋራ ግንዛቤ እንዲኖረን ለማድረግ እሞክራለሁ።

- ኢትዮጵያ ዉስጥ አቶ አባንግ ሜቶ ብዙ ጊዜ እንደሚሉት 99% በመቶ ኢትዮጵያዊ የለም። ሁሉም 100% ኢትዮጵያዊ ነዉ። አንዱ ከሌላዉ የበለጠ ለኢትዮጵያ ሃሳቢና ኢትዮጵያዊ የሚወድ ተደርጎ ሊቆጠር አይችልም። አንድ ሰዉ እኔ “ኦሮሞ ነኝ” ወይም “ትግሬ ነኝ” ወይም “አማራ ነኝ” ሊል ይችላል። ነገር ግን ትግሬ ነኝ ወይም ኦሮሞ ነኝ ማለቱ ኢትዮጵያዊነቱን አይቀንስም። የፈለገዉ ጎሳ አባል ይሁን፣ ያ ሰዉ ከማንም ያልተናነሰ ኢትዮጵያዊ ነዉ። ኢትዮጵያዊ አይደለሁም እንኳን ቢል ኢትዮጵያዊ ነዉ።

  ኢትዮጵያዊነት የጋራ ሃብታችን ነዉ። ኢትዮጵያዊነት የሚያስተሳስረንና የሚያያይዘን ነዉ። ኢትዮጵያ ስትከፋፈል፣ ስትወደቅ፣ በጦርነት ስትታመስ ፣ ስትደኸይና ለረሃብ ስትጋለጥ ..ትግሬዉም፣ አማራዉም ኦሮሞዉም፣ ድብልቁም ሁሉም ነዉ የሚጎዳዉ።

  ኢትዮጵያ የሁላችንም ናት። ዶ/ር ቡልቻ ደመቅሳ ፓርላማ በጥግ በኩል ተቀምጠዉ « ኢትዮጵያ የኢሕአዴግ ብቻ አይደለችም። ኢትዮጵያ የሁላችንም ናት» እንዳሉት ኢትዮጵያ የሁላችንም ናት። የኢትዮጵያ ጥንካሬና አንድነት ለኦሮሞዉ ለትግሬዉ ለአማራዉ ለጉራጌዉም ለሁሉ ጥቅም ነዉ።

- አንድ ሰዉ ትግሬነትን ወይም ጉራጌነት እያጎላ ቢናገር ኢትዮጵያዊነቱን መቀነስ እንዳልሆነ ሁሉ አንድ ሰዉ «ኢትዮጵያዊነት ነዉ ዘሬ ፣ ኢትዮጵያዊነት ነዉ ብሄሬ፣ ኢትዮጵያዊነት ነዉ ብሄረሰቤ» ብሎ ቢናገር የብሄር ብሄረሰብ መብትን መጋፋት ወይን ደግሞ ነፍጠኝነት ተደርጎ መወሰድ የለበትም። ወይንም አንድ ሰዉ ሕብረ ብሄረ ከሆነ ወይንም ኢትዮጵያዊነትን ካጎላ እንደ “አማራ” መቆጠር ትልቅ ስህተት ነዉ። ኢትዮጵያዊነትን ለ”አማራ” ብቻ የሰጠዉ ማን ነዉ ?

  ለምሳሌ አሁንም እንደገና ዶር ቡልቻን ልጥቀስና በዉጭ አገር ላለ ሬዲዮ «ቅንጅት የአማራ ድርጅት ነዉ» ሲሉ ነበር ስለቅንጅት አስተያየት የሰጡት። ዶ/ር ቡላቻ (ይቅርታ እንደሚያደርጉልኝ ተስፋ አደርጋለሁ) በጣም እንደተሳሳቱ ልነግራቸዉ እወዳለሁ። እርሳቸዉ ከፈለጉ «እኔ ኦሮሞ ነኝ፤ የኔ ድርጅት የኦሮሞ ድርጅት ነዉ» ማለት ይችላሉ። ነገር ግን አባል ያልሆኑበትን ድርጅት አዉርደዉ «የአማራ ድርጅት ነዉ» ማለት ትልቅ ስህተት ነዉ። የቀድሞ ቅንጅት አሁን ደግሞ የአንድነት ደጋፊዎችን በዚህ አባባላቸዉ እንዳሳዘኑ ጥርጥር የለኝም።

  በቅንጅት ዉስጥም ሆነ በአንድነት ዉስጥ በርካታ ኢትዮጵያዉያን አሉ። «በዘራችን ከመለየት ይልቅ በኢትዮጵያዊነታችን መለየት ነዉ የምንፈልገዉ፣ የዘር ፖለቲካ አያዋጣንም» በሚል፣ ከአገሪቷ ክልሎች ሁሉ የተወጣጡ ዜጎች ያሉበት ድርጅት ነዉ። አንድ ድርጅት «ኦሮሞ» የሚል ስያሜ ከሌለበት የኦሮሞ አይደለም ብሎ ማሰብ አይቻለም። አንድነት፣ መኢአድ፣ ኢዴፓ ... የመሳሰሉ ሕብረ ብሄር ድርጅቶች ከኦነግና ከኦሮሞ ፌደራሊስት ንቅናቄ ባልተናነሰ ለኦሮሞዉ መብት የቆሙ ናቸዉ። ከሕወሃትና ከአረና ትግራይ ባልተናነሰ ለትግሬዉ የቆሙ ናቸዉ።

- ኢትዮጵያ አገራችን ያለፉት ታሪኮቿ ከሞላ ጎደል የጦርነትና የደም መፋሰስ ታሪክ ነዉ። ይህ እርስ በርስ የመጠቃቃት፣ ለጥፋት የመፈላለግ፣ እርስ በርስ የመጠላላትና ያለመተማመን ባህላችንን መቀየር መቻል አለበን። ከኛ የተለየ ሃሳብ ሊኖራቸዉ ቢችልም ከሌሎች ኢትዮጵያዉያን ጋር መነጋገር ያስፈልጋል። ካልተነጋገርን፣ በጋራ ችግራችንን ካልፈታን፣ ዘለቄታ ያለዉ ሰላምና እድገት በኢትዮጵያ ሊኖር አይችላም። አንዳችን አንዳችንን መቀበል ካቃተን ኢትዮጵያ የምትባል አገር አትኖርም። ሁላችንም እንጠፋለን።

  መነጋገር፣ መወያየትና መመካከር ካልቻለን፣ «ምንድን ነዉ የሚያጣላን ? ምንድን ነዉ በመካከላችን ያለዉ ችግር ? » ብለን መቀራረብን በመሃከላችን ካላመጣን ወደፊት በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ነዉ የሚፈጠረዉ።

- ለሕግ የበላይነት መገዛት በጣም አስፈላጊ ነዉ። ብዙ ጊዜ ግለሰቦችን «ወንጀለኞች ናቸዉ። ግፍ ሰርተዋል ይቅርታ መጠየቅ አለባቸዉ» ሲሉ አንዳንዶች ይሰማሉ። ለምሳሌ እነ አቶ ስዬ አብርሃ፣ አቶ ገብሩ፣ ዶር ነጋሶ የመሳሰሉት ላይ እየተነሱ ያሉ ክሶች መጠናቸዉ ይችን ሰሞን እየጨመረ ነዉ። አቶ ስዬ አብርሃና ዶር ነጋሶ ጊዳዳ የአንድነት ለዲሞርክራሲና ለፍትህ ፓርቲ በጠራዉ ስብሰባ ላይ ንግግር ማደረጋቸዉ ያስቆጣቸዉ ቁጥራቸዉ ትንሽ አይደለም። «እንዴት ለወንጀለኞ አንድነት መድረክ ይሰጣል? » ሲሉም አንዳንዶች ተቃዉሞ ሲያቀርቡ ስምቻለሁ።

  አገሬን በስደት የለቀኩት ኢሕአዴግ ስልጣን በጨበጣ በአንድ አመት ጊዜ ዉስጥ ነዉ። የኢትዮጵያን ጉዳይ በጥልቀት መከታተል የጀመርኩት ደግሞ ከምርጫ 97 በኋላ ነዉ። አቶ ስዬ ሆነ ዶር ነጋሶ ምን ያደርጉ እንደነበረ እምብዛም አላወቅም። በመሆኑ ወንጀለኛ ናቸዉ አይደሉም ብዬ መከራከር አልችለም። እርግጥ የኢሕአዴግ ከፍተኛ አመራር ስለነበሩ ኢሕአዴግ ላጠፋዉ ስህተት ተጠያቂ መሆናቸዉን የሚዘነጉት አይመስለኝም።

  እነ አቶ ስዬ ብቻ ሳይሆን ለኤርትራ መገንጠልና በዚያን ወቅት ለነበረዉ ከፋፋይ የዘር ፖለቲካ ተግባራዊ መሆን፣ ያኔ የኢሕአዴግ ባለሥልጣን አሁን ደግሞ የግንቦት ሰባት መሪ የነበሩ አቶ አንዳርጋቸዉ፣ የሕብረት መሪ ዶር በየነ ጵጥሮስ፣ የኦነግ መሪዎች ... ሁሉም ተጠያቂ ናቸዉ። ኢሕአፓ እራሷ የ66ቱ አብዮት የፈነዳ ሰሞን ያኔ ታራምዳቸዉ የነበሩ አንዳንድ የተሳሳቱ ፕሮግራሞችም ነበሯት።

  እንግዲህ እንወቃቀስ ከተባላ ገመዱ እየረዘመ ነዉ የሚመጣዉ። ሁላችንም እንዳጠፋን እንደተሳሳትን አዉቀን በጋራ አገራችን ኢትዮጵያ ካላችበት አዘቅት ዉስጥ ማዉጣት ይጠበቅብናል። ወደ ኃላ እየተመለከትን ያላፈዉ ታሪካችን እግራችንን እየጠለፈ ወደፊት እንዳንራመድ ሊያግደን አይገባም።

  ይህን ስል ሰዉ የገደሉ ወይንም ያስገደሉ፣ በእጃቸው ደም ያላባቸዉ ሰዎች ለፍርድ አይቅረቡ ማለቴ አይደለም። የኢሕአዴግ፣ የኦነግ፣ የኢሕአፓ፣ የመኢሶን፣ የደርግም ሆነ የማናቸዉም የፖለቲካ ፓርቲ አባል ይሁኑ ሰዎች በእጃቸዉ ደም ካለባቸዉ ለፍርድ መቅረባቸዉ አጠያያቂና አከራካሪ አይደለም። በዚህ ልንስማማ ይገባል። ይቅርታና ፍትህ አብረዉ የሚሄዱ ናቸዉ። «ይቅርታ እንደራረግ» ስንል ደማቸዉ የፈሰሰ፣ በግፍ የተሰቃዩ ፍትህ አያግኙ ማለት አይደለም።

  «ታዲያ ወንጀለኞች እንዴት ነዉ ተጠያቂ የሚሆኑት ?» የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። አንድ ሰዉ የኢሕአዴግ ባላሥልጣን ስለነበረ ብቻ ወንጀለኛ ነዉ ብሎ መደምደም ትልቅ ስህተት ነዉ። ነጻ በሆነ የፍርድ ሂደት ክስ ቀርቦበት፣ እራሱን የመመከት እድል አግኝቶ ጥፋተኛ እስካልተባለ ድረስ፣ ማንም ሰዉ ጥፋተኛ ተብሎ ሊፈረጅ አይገባም።

  እነ አቶ ስዬን እንደወንጀለኛ የሚቆጥሩ ሰዎች መረጃ ካላችዉ ማድረግ የሚኖርባቸዉ እነዚህን ሰዎች በሕግ መክሰስ ነዉ። አቶ ስዬ፣ አቶ ገብሩና ዶር ነጋሶም በማናቸዉም ጊዜ ክስ ከቀረበባቸዉ ለፍርድ ለመቀረብ ዝግጁ እንደሆኑና አገር ለቀዉ እንደማይሄዱ ሲናገሩ የሰማሁ ይመስለኛል። ስለዚህ በስሜት «እገሌ ወንጀለና ነዉ፤ እገሌ እንደዚህ ነዉ፣ እገሌ ይቅርታ ይጠይቅ» ከማለታችን በፊት ወንጀል የሰሩ በሕግ ይጠይቁ ዘንድ በአገራችን ፍትሃዊ የሕግ ስርዓት እንዲዘረጋ በጋራ መታገል አለበን። አለበለዚያ ከፈረሱ በፊት ጋሪዉን እንደማስቀደም ነዉ።

በተቃዋሚ ወገን የሆኑ የሚደነቁና አገር ወዳድ ተደርገዉ የሚቆጠሩ ሰዎች፣ እኛ የማናወቀዉ የሰሩት ወንጀል ሊኖር ይችላል። በዉጭ አገር ተሰደዉ ሲኖሩ አገር ቤት ምን ያደርጉ እንደነበረ ብዙዎቹን አናወቅም። ለምሳሌ በዳያስፖራዉ እንቅስቃሴ ትልቅ አስተዋጾ የሚያደርጉ በግል የማወቃቸዉ አንድ ሰዉ አሉ ። እኚህ ሰዉ በደርግ ጊዜ የቀበሌያችን ሊቀመንበር ነበሩ። «ያለዉ ወደ ቦሌ ፣ ደሃዉ ወደ ጦሌ" በሚባልበት ወቅት ብሄራዊ ዉትድርና እየተባለ የድሃ ልጆች በግድ ወደ ጦሌና ታጠቅ ..ማሰልጠኛ ጣቢያ ይወሰዱ ነበር።

እኚህ ሰዉ ከአብዮት ጠባቂ ሊቀመንበር ከነበሩት ጋር በመሆን በየደሃዉ ቤት እንደ ወንበዴ እየገቡ፣ እናቶቻችንን ኢትዮጵያዊ ጨዋነት በጎደለዉ መልኩ እየተሳደቡ ትልቅ ሽብር ይፈጥሩ የነበሩ ሰዉ ናቸዉ። ሁሉም የራሱ ጉድ በጓዳዉ ተሸክሟል ማለቴ ነዉ።

ዶ/ር አለማየሁ ገብረማሪያም በሎስ አንጀለስ በቅርብ በተደረገዉ ስብሰባ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረዉን "ከናንተ ሐጢያት የሌለበት የመጀመሪያዉን ድንጋይ ይወርዉር" የሚለዉን አባባል ጠቅሰዉ ነበር። ትልቅ አባባል ነዉ። አሁን እርስ በርስ ከመወነጃጀል ፍርዱን ለእግዚአብሄርና ለሕግ መተዉ የሚበጅ ይመስለኛስል።

እንግዲህ ከላይ የተዘረዘሩ መሰረታዊ ጭብጦችን ካየን ዘንዳ አሁን መድረክ ስለተባለዉ አካል ያሉኝን አንዳንድ አስተያየቶች ለአንባቢያ ላከፍል።

አቶ ስዬና ዶር ነጋሶ ጊዳዳ በግለሰብ ደረጃ፣ እንዲሁም አራት ድርጅቶች በጋር መድረክ የተሰኘ አካል በሰኔ ወር 2000 መመስረታቸዉ ይታወሳል። በመስከረም 2001 በወጣ ሕግ መሰረት፣ ፓርቲዎች በቅንጅት ወይንም ግንባር ወይንም ሕብረት ካልሆነ በቀር መድረክ በሚል እንዲሰባሰቡ ሕጉ ስለማይፈቅድ አሁን መድረክ የሚባል ሕጋዊ አካል የለም።

መድረክ የሚባል የነበረዉ አካል ዉስጥ የነበሩ ድርጅቶችና ግለሰቦች በጋራ ዉይይታቸዉንና ምክክራቸዉ ቀጥለዋል። «አንድነት መድረክን ተቀላቀለ» ተብሎ ሲወራ መድረክ ከነበሩ ድርጅቶች ጋር አብሮ በጋራ መስራት የሚቻልበትን ሁኔታ አንጥሮ ለማዉጣት ዉይይት ጀመረ ማለት ነዉ እንጂ፣ በሕግ የታወቀ አንድ ሕጋዊ አካልን ተቀላቀለ ማለት እንዳልሆነ ነዉ የገባኝ፣ አቶ አሥራት ጣሴ በቅር ባደረጉት ቃለ ምልልስ በመነሳት። እንግዲህ በልማድ መድረክ ሲባል ወይንም በዚች መጣጥፍ መድረክ ብዬ ስጽፍ፣ አንድ ሕልወና ያለዉ ሕጋዊ አካልን ማለቴ አይደለም። ነገር ግን ከቀድሞ የመድረክ አባላት ጋር ዉይይት የማድረጉን ሂደት እንጂ።

አቶ ስዬ «አማካኝ ስፍራ እንፈልግ» በሚል አርእስት ስር ሲጽፉ ፡ "የፖለቲካ ልምዳችን በጋራ አሸናፊ ሆኖ መዉጣት አላስተማረንም። ይልቁንስ ድምሩ ዜሮ የሆነ ጨዋታ ያስተማረን በመሆኑ ለኛ ኢትዮጵያዉያን በጋራ እምነቶቻችንና ተስፍዎች ዙሪያ ተሰባስቦና ልዩነቶችንም አቻችሎ መሄድ ቀላል ፈተና እንደማይሆን ይገመታል። ይሁን እንጂ ሊያልፉት የማይቻል ፈተና አይሆንም። ይህንን ሳያሳኩ ኢሕአድደዴ የመተካትና በኢትዮጵያ ዲሞክራሲን የማስፈኑን ዳገት መዉጣት እንደማይቻል ሳይታለም የተፈታ ነዉ» ብለዉ ነበር።

ትልቅና ብስለት ያለዉ አባባል ነዉ። በርግጥ የኛ ኢትዮጵያዉያን መነጋገርና አብሮ በጋራ መሥራት ብቻ ነዉ ለአገራችን ዘለቄታ ያለዉ መፍትሄ የሚያመጣዉ። ልዩነቶች ይኖራሉ። ከአንዳንድ የመድረክ አባላት የተሰሳተ አባባሎች ልንሰማ እንችላለን። ግን ልዩነቶቻችን ለማጥበብ መነጋገር በጣም አስፈላጊ ነዉ። በመነጋገር መተማመን ይመጣል። መነጋገራችንና መስማማት በምንችላቸዉ ነገሮች አብሮ መሥራታችን ለእድገታችን ቁልፍ ነዉ።

የቅንጅት መሪዎች በቃሊቲ በነበሩ ጊዜ የዳያስፖራዉ ቅንጅት ከኦነግና በኡብነግ ጋር በመሆን ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ የሚል አካል ፈጥረዉ ነበር። ይህ አካል ከጅምሩ ፣ደጋፊዎችን በማወያየት እንዲሁም ዲሞክራሲያዊና ግልጽ በሆነ መንገድ ሳይሆን በሚስጥር በጥቂቶች ብቻ ተጠንስሶ የመጣ አካል ስለነበረ፣ ምንም እንኳን በመርህ ደረጃ የተለያዩ ኢትዮጵያዉያን በአንድ ላይ መምጣታቸው የሚያስደስት ቢሆንም፣ ሰላማዊ ትግል የሚያደርግ በጠመንጃ ከሚታገል ጋር የመሥራቱ ነገር ዉስብስብ በመሆኑ እንዲሁም የኢትዮጵያ አንድነት በዚህ አካል በማያሻማ መልኩ ባለመቀመጡ ከፍተኛ ተቃዉሞ ሊደርስባት ችሏል። በዚህም ምክንያት ትልቅ ደረጃ ሊደርስ የሚችል አካል በእንጭጭነቱ ለመሞት በቃ።

በዚያን ወቅት በአጭር አድሜዉ ይህ አካል፣ በኦሮሞ፣ ሶማሌ አክራሪዎችና በተቀረዉ ኢትዮጵያዉያን ዘንድ ትልቅ መቀራረብን ፈጥሮ እንደነበረ ይነገርለታል። አንድ አትላንታ ያለ ወዳጄ ሲነግረኝ «ከዚህ በፊት እንደ ባእድ ዜጋ የማንነጋገር የኦሮሞ አክራሪዎች ከኤኤፍዲ ምስረታ በኋላ መቀራረብ ጀመርን» ብሎ ነበር የነገረኝ።

እንግዲህ አስቡት ያኔ በጣም አክራሪ ከነበሩና በኢትዮጵያ አንድነት እንደሚያምኑ በይፋ ግልጽ ካላደረጉ አካላት ጋር በተደረገ አንጻራዊ መቀራረብ ብዙ አዋንታዊ የሆኑ ነገሮች ታይተዉ ነበር።

ታዲያ አሁን በተለይም ደግሞ ከነ ኦነግ ጋር ተደርጎ የነበረዉን ኤኤፍዲ ይደግፉ ከነበሩ ወገኖች መድረክ ላይ ተቃዉሞ ሲነሳ ማየቱ አስገርሞኛል። እነዚህ ሰዎች መድረክ ዉስጥ ያሉ ሰዎችን በግለሰብ ደረጃ ስለሚጠሉ እንጂ ኤኤፍዲን ደግፈዉ መድረክን የሚቃወሙበት ሎጂክ አላቸዉ ብዬ አላስብም።

ያኔም ኤኤፍዲን ይቃወሙ ለነበሩ ወይንም በተለያዩ ምክንያት የአንድነት አንኳር መርህዎች ሊሳሱ ይችላሉ ብለዉ ለሚፈሩ ወገኖች «ፍርሃታቹህና ጭንቀታቹህ ተገቢ ነዉ» በማለት አራት ነጥቦችን ላካፍላቸዉ እወዳለሁ።

- በመድረክ የነበሩ ድርጅቶች ያለ አንዳች ማቅማማት ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት የቆመ ናቸዉ።

- መድረክ ዉስጥ ያሉ የብሄር ድርጅቶች ለብሄር መብት የቆሙም ቢሆን አክራሪ ያልሆኑ፣ በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምኑና ደጋፊ ያላቸዉ ድርጅቶች ናቸዉ። በብሄር መደራጀታቸዉ ያነሱ ኢትዮጵያዉያን አያደርጋቸዉም። በመድረክ ስር ለመሰባሰብ ሲመጡም ከብሄር ዉክልናቸዉ አልፈዉ በአገር ደረጃ ለዉጥ ለማምጣት፣ አንዲ ዴሞክራሲያዊት ፣ ለሁሉም ልጆቿ እኩል የሆነች ኢትዮጵያን መገንባት ስለፈለጉ እንደሆነ በግልጽ ያሳያል።

- በመድረክ የነበሩ ድርጅቶች የአሰብ ወደብ ለኢትዮጵያ መሰጠት አለበት ብሉ አጥብቆ የሚያምኑና በሰላማዊ መንገድ ኢትዮጵያ የባህር ወደብ እንዲኖራት ይፈልጋሉ።

- «መድረክ» በጋራ ለምርጫ መወዳደር ማለት አይደለም። ለምርጫ ከመወዳደር በፊት የዲሞክራሲ ተቋማት ነጻና ገለልተኛ እንዲሆኑ ያስፈልጋል። እንደነ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ አይነት አንጋፋ የሕሊና እሥረኞች መፈታት አለባቸዉ። የፖለቲካ ድርጅቶች ያለወከባ መንቀሳቀስ መቻል ይኖርባቸዋል። መድረክ ዋና አላማዉ እንግዲህ እነዚህ ለምርጫ የሚያስፈልጉትን አበይት ነገሮች ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ ነዉ። «ምን ተይዞ ጉዞ» እንደሚባለዉ የምርጫ ነገር በኋላ የሚመጣ ጉዳይ ነዉ።

  ለምርጫ የሚያስፈልግ ተቋማት በደንብ ከተደራጁ በኋላ፣ ያኔ ምርጫዉን መወዳደር ይቻላል። የዚያን ጊዜ አብረዉ በመድርክ ሥር ሲሰሩ የነበሩ ድርጅቶች በግላቸዉ የምርጫ ዘምቻቸዉን ያደርጋሉ። ለምሳሌ የአንድነት ፓርቲ አንቀጽ 39 ከሚቀበሉ ድርጅቶች ጋር በጋራ ለምርጫ ሊቀርብ አይችልም። አንቀጽ 39ን የሚቃወምም ሆነ የሚደግፍ በፊናዉ የፖለቲካ ፕሮግራሙን ያስተዋዉቃል። በፖለቲካ ፕሮግራማቸዉ የተቀራረቡ ዉህደት ፈጥረዉ በጋራ ሊቀርቡ ይችላሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብም ያኔ ይወስናል። ስለዚህ አሁን እንደ አንቀጽ 39 አይነቶቹን ማንሳት ዱቄት ሳይፈጭ ሳይቦካ ሳይጋገር እንጀራ እንብላ ማለት ነዉ።

መድረክ ዉስጥ የነበሩ አራት ድርጅቶች እንዲሁም አንድነት ጨምሮ ሁለት ሕብረ ብሄር ድርጅቶች፣ በአሁን ወቅት በጋራ መሥራት የሚችሉበትን ሁኔታ እየቀየሱ ናቸዉ። አቶ ስዬ አብርሃና ዶር ነጋዶ ጊዳዳ ከአሁን በኋላ በግለሰብ ደረጃ ሊንቀሳቀሱ አይችሉም። ሕጉ አይፈቅድላቸዉም። የራሳቸዉ ፓርቲ ይመስርታሉ ወይንም ከዚህ በፊት የነበሩ ፓርቲዎችን ይቀላቀላሉ።

ዶር ነጋሶ በቅንጅት ስዊዘርላንድ ፓልቶክ ክፍል ከዚህ በፊት ቀርበዉ በነበረ ጊዜ ከሰማኋቸዉ በመነሳት፣ በኢትዮጵያ አንድነት ቢያምኑም የኦሮሞ ሕዝብ የራሱን እድል በራሱ መወሰን አለበት ብለዉ ያምናሉ። «የኦሮሙ ሕዝብ ሬፈረንደም ያድርግ፡ እኔም ከኢትዮጵያ ጋር እንዲሆን ዘመቻ አደርጋለሁ» ነዉ ዶር ነጋሶ የሚሉት። (በፍጹም ተቀባይነት ሊኖረዉ የማይችል አባባል) ስለዚህ የኦሮሞ ሕዝብ ዉሳኔዉን እስካልሰጠ ድረስ በሕብረ

ብሄር ድርጅት መታቀፉ ላይመቻቸዉ ይችላል ብዬ አስባለሁ። እነ ዶር ቡላቻ ደመቅሳን ይቀላቀላሉ የሚል ግምትም አለኝ።

አቶ ስዬ አብርሃን በተመለከተ የአረና ትግራይ አባል እንደሆኑ የሚያስቡ አሉ። አቶ ስዬ ግን እስከአሁን ድረስ በክልል የተደረጃዉንና ጓደኞቻቸዉ ያቋቋሙትን አረና ትግራይ አልተቀላቀሉም። በብሄር ወይም ክልል ከመደራጀት በሕብረ ብሄርነት መደራጀትን የሚፈልጉ ይመስላል።

«የአንድ ብሄር ተወላጆች ተሰባጥረዉ በሚኖሩበት አካባቢ የአንድን ብሄር ተወላጅ ብቻ እየመለመሉ ሌላዉን የመተዉ ባህሪ ስላለዉ ለሁሉም ዜጎች ተዳራሽ ያለመሆኑ ችግር አለዉ። በጋራ የሚኖሩ የጋራ ብሶት ያላቸዉን ዜጎች በጋራ ለማታጋል አስቸጋሪነት ስላለዉ በከተሞችና ተቀላቅለዉ በሚኖሩ ዜጎች አካባቢ የዚህ ብሄር ተወላጅ ነኝ ብለዉ ሊፈረጁ በማይፈልጉና በሚቸገሩ ኢትዮጵያዉያን ዘንድ ይሄ አደረጃጀት ተዳራሽ ያለመሆን ችግር አለበት» ብለዉ የጻፉትን «አማካኝ ስፍራ እንፈልግ» በሚለዉ ጽሁፋቸዉ አንብቢያለሁ።

«የመገንጠል መብት አያስፈልግም። የብሄር ብሔረሰስበ መብት መከበር ቢኖርበትም የግልሰብን መብትን እስካልተጋፋ ድረስ ነዉ መሆን ያለበት» ወደ ሚል እምነት አቶ ስዬ መጥተዉ ከሆኑ የአባልነት ማመልከቻቸዉን ለአንድነት ዲሞክራሲና ለፍትሃ ፓርቲ ቢያስገቡ እኔ በበኩሌ በአዋንታዊነት ነዉ የምቀበለዉ።

እግዚአብሄር አገራችን ኢትዮጵያን ይባርካታ !
አንድ ኢትዮጵያ አንድ ሕዝብ !

www.ethiomedia.com